# የሞተስ ሌላ!

*በላይነህ አባተ (abatebelai@yahoo.com)* *ሚያዚያ ሁለት ሺህ አንድ ዓ.ም.*

ለምን እንደሆነ አላውቅም በአለፉት አስራ-አምስት አመታት ውስጥ ለሰብአዊ መብት መከበርና ለአገራቸው እድገት መልካም ተግባራትን የፈጸሙ አቻ የሌላቸው አያሌ የጦቢያ ልጆች ከዚህ አለም በሞት ተለዩ። ትዝ እንደሚላችሁ በአገራችን ባህል አንድ ሰው ሲሞት ለቅሶ የሚለቀሰው በዚያን ወቅት ለሞተው ሰው ብቻ ሳይሆን ከብዙ አመታት በፊት ለሞቱትም ዘመዶች፣ ወዳጆች፣ ጎረቢቶችና መልካም ለሰሩ የአገር ሰዎችም ጭምር ነው። *"ዋይ ዋይ ሲሉ የርሃብን ጉንፋን ሲስሉ"* እያለ አንጀታቸውን ለተሰለቡት፣ ጎራሯቸው ለደረቀውና በሰው ሰራሽ ድርቅ ላለቁት ኢትዮጵያውያን የድረሱላቸው ጥሪ ያንጎራጎረው አንደበት በቅርቡ እስከ ፍጻሜው ሽልብ ማለቱን በሰማሁ ጊዜም በተፈጥሮ ምክንያትም ሆነ በአረመኔ ገዥዎች እጅ ክንዳቸውን የተንተራሱትን ብዙዎቹን የተከበሩ ጦቢያውያንን አስታወስኩ። መላእክት በገነት ስማቸውን ያንሷቸውና ሀዲስ፣ አስራት፣ ጸጋዬ፣ መኮንን፣ ወዘተርፈ እያልኩ የልጆቿን ስም ጠርታ እንደማትጠግብ እናት ስም መደረደሩን ቀጠልኩ። አንዴ ከተጀመረ ማለቂያ የለውምና ትንሽ ወደ ኋላ ተጉዤም ከሚያሸማቅቅ የባርነት ታሪክ ገላግለውን የኖሩትን እነ አብዲሳ አጋን፣ ዘርዓይ ደረሰን፣ ለጀግንነቱ ገመድ እንደ ወርቅ ሜዳሊያ አጥልቀንለት ያለፈውን በላይ ዘለቀን፤ እንደዚሁም ከዘመኑ ካህናት እጅግ በተለየ መንገድ ለፍትህ ሲሉ እንደ ክርስቶስ አንገታቸውን የሰጡትን አቡነ ጴጥሮስንም አስታወስኩ። በዚህም አላቆምኩ። ላገራቸው መሻሻል ሲለፉ ኖረውና በጎ ተመኝተው መልካም ሳያዩ ያለፉትን ጦቢያውያን ሁሉ የምችለውን ያህል በህሊናዬ አወጣሁና አወረድኩ።

እንደምትገነዘቡት አዛኝ ሲያዝን ይቆይና ሲደክመው ራሱን በራሱ ማጽናናት ይጀምራል። እኔም እንደዚሁ ሐዘን የተቀላቀለበት ስሜቴ ታገስ ሲልልኝ "ለመሆኑ እነዚህ ለሰው ልጅ ልእልናና ለአገር ክብር ሲማስኑ የኖሩ ሰዎች ቢሞቱ ለራሳቸው የቀረባቸው ነገር ምንድነው?" ብዬ እንደ ሞኝ ራሴን በራሴ ጠየኩ። እውነቴን ነው! ምንድነው የቀረባቸው? በሃያ አንደኛው ክፍለ-ዘመን በምድረ ጦቢያ ሕዝብ ሐሳቡን በመግለጹ ሲገደል፣ ሲታሰር፣ ሲሰወር፣ ሲሰደድና ንብረቱን ሲቀማ ነጋ ጠባ ማየት? ወንድሙ ወንድሙን፤ እህትም እህቷን እየጠቆሙ ለገዳዮች ሲያቀብሉ ማስተዋል? በመንኮራኩር አገናኝነት አስሩ ፕላኔቶች አንድ እየሆኑ በመጡበት ዘመን ለበርካታ ሺዎች ዘመናት መከራውንም ደስታውንም በመካፈል አብረው የኖሩ ጦቢያውያን በቋንቋ ቢላዋ በግድ ሲሰነጣጠቁ መመልከት? ሕዝባቸው የሚበላው የሚጠጣው አጥቶ የትንሹም የትልቁም አለም መዘባበቻ ሲሆን መስማት? ገዥዎቻቸው ክብራቸውን ሸጠው የባእዳን ተራ ተላላኪ ሲሆኑ መመልከት? ከአለም መጀመሪያ የተፈጠረች አገራቸው በችጋር፣ በበሽታና በማይምነት አንደኛ፤ በኢኮኖሚ እድገት ደግሞ ውራ ወጣች የሚለውን የሚዘገንን ዜና በሄዱበት ሁሉ መስማት? እኮ ምንድነው የቀረባቸው? እንደ እውነቱ ከሆነ የቀረብንስ እኛ! አዎ ከእነዚህ ሁሉ ኋላ ቀር ችግሮች ነቅሎ የሚያወጣ ጀግና ያጣንስ እኛ! ብሶታችንን ከልብና ከአንጀታችን እያወጣ የሚገልጽልን ደራሲ፣ ገጣሚ፣ ሙዚቀኛ፣ ምሁር ያጣንስ እኛ! ነፍስ ስናጠፋ፣ ስናጭበረብር፣ ስንክድ፣ ህግንና የሽምግልናን ደንብ ስናፈርስ የሚገስጽ የነፍስ አባት ያጣንስ እኛ! እነሱማ የቀረባቸው ሌተ ተቀን ለአገራቸው መጨነቅ፣ እንቅልፍ አጥተው ሲጽፉ፣ ዜማ ሲያወጡ ማደር፤ ይህንን በማድረጋቸውም በባለጌዎች መዘለፍ፣ መደብደብ፣ እንዲያም ሲል መሰደድ፣ መታሰርና መገደል አይደለም እንዴ? ያለጥርጥር የቀረብንስ እኛ ነን! ማልቀስ ያለብንም ለነሱ ሞት ሳይሆን ወግና ማእረግ ያለው ሰው ለማይበረክትልን ለእኛው ለራሳችን ነው።

እየቆየሁ ሲሄድና መጽናናቴ እየበረታ ሲመጣ ደግሞ "እነሱ አልሞቱም! የሞተስ ሌላ!" ብሎ አእምሮዬ በሐይለ-ቃል ነገረኛና አረፈው። ምናልባት አእምሮዬ እውነቱ ነው! የትኛው ጎበዝ ነው አቡነ ጴጥሮስ የሉም፤ ሀዲስ አለማየሁ አረፈ፤ ጸጋዬ ገብረ መድህን ወይም ጥላሁን ገሰሰ ሞተ ብሎ መናገር የሚደፍረው? መሬቷ ለባርነት እጅ እንዳትሰጥ የገዘተ፣ ለሕዝብ ልእልና እጁ ዉሀ እስቲቋጥር የጻፈ ወይም ልሳኑ እስኪዘጋ ያዜመ ሳይሆን ለዘላለም የሞተስ ለስልጣንና ለገንዘብ ብሎ የወንድሞቹን ደም ያፈሰሰ ወይም ቢላዋ ያቀበለ ነው። እስከፍጻሜው ክንችር ያለስ እንደ ጠማማው እንጨት ከምሳር ውስጥ ገብቶ የራሱን ወገን የሚያስፈጅ የሰው ታናሽ! እየሄደና እየበላ የሞተስ ነፍሰ-ገዳይን መገዘት ያልፈለገውና ለአስራት ከፋይ ሟችም ጸሎት የሚነፍገው ቆብ የደፋና መስቀል ያንጠለጠለ ካህን! በቁሙ የሞተስ ጀግኖችና ጠቢባን ባስረከቡት ምድር ላይ ተንፈላሶ ሆዱን ብቻ እየሞላ ሌላ ምንም ነገር ሳይሰራ እድሜውን የሚገፋ የኔ ቢጤው ሰው-መሳይ! በፍጹም እነሱስ አልሞቱም! የሞተስ ገላው መሬት ሲገባ ከመሬት በላይ የሚቀር ነገር የሌለው፣ የራስ ቅሉን ከህሊና ሳይሆን ከሆዱ ጋር በሙጫ ያጣበቀ የኔ አይነቱ ለሆዱ ብቻ አዳሪ! ደጋግሞ ሙትት ያለስ እንደ አረመኔው ሂትለር በዚህኛውም ሆነ በዚያኛውም አለም ሲረገም የሚኖረው የልጅ የአዋቂው ነፈሰ-ገዳይ! አዎ እነሱስ አልሞቱም! የሞተስ ባለበት አለ! አዎ የሞተስ ሌላ! ሌላ… ሌላ…

ለሰው ልጅ መብትና ክብር ድምቻውን አሰምተው ያለፉትን ሁሉ ስጋቸውን ብዕር ነፍሳቸውን ደግሞ ፈጣሪ ለዘላለም ያወድሰው!

*ከዚህ በፊት የተደረሱ ተመሳሳይ መልእክቶች*

1. *ሞትም ወንድ መራጭ ነው!* http://addisvoice.com/poems/motimw.pdf
   http://www.quatero.net/gitem/MotimWondMerachNaw.pdf
2. *ምኑን ሰው ሆንኩ!* http://www.abbaymedia.com/Amharic/saaw.pdf

3. *ለመሆኑ ሰው ምንድነው?* www.addisvoice.com/article/sew2.pdf